# የመጽሐፍ ትችት፤ "እኛና አብዮቱ"

በጥበበ ሣሙኤል ፈረንጅ፡፡ (ክፍል አንድ)

ባለፉት ጥቂት ዓመታት፤ በርካታ ኢትዮጵውያን ስለሃገራችን ታሪክ፤ መጽሃፍት እየፃፉ ነው፤ ይህም እሰየው የሚያሰኝ ጅማሮ ነው ፡፡ በተለይም በታሪኩ ውስጥ እራሳቸው ተዋንያን የነበሩ ሰዎች፤ ታሪካችንን ሲጽፉ፤ ከሚሰጡን የመጀመርያ ደረጃ መረጃ በመነሳት ስለሚጽፉ፤ በሰሚ-ሰሚ ከሚጻፉት መጽሃፎች የተሻለ ይዘት ይገኝባቸዋል፡፡ ሆኖም ጸሃፊዎቹ፤ በታሪኩ ውስጥ ተዋንያን የነበሩ ይሁኑ እንጂ፤ ብዙዎቹ የታሪክ ምሁራን ካለመሆናቸውና፤ የራሳቸውን የግል ፍላጎትና ስሜት ስለሚያንጸባርቁም፤ የሚፅፉት ሁሉ ትክክለኛ የሆነ የታሪክ ፋይዳ አለው ብዬ አላምንም፡፡ ዛሬም ከታሪክ ይልቅ የራሳቸውን የፖለቲካ አሻራ ለመጣልና፤ የነበራቸውንም እኩይ ሚና ለመሸፈን ሲሉ እውነቱን አጣመው፤ ደብቀውና የሰሩትን ዲያቢሎስያዊ ስራ፤ የተቀደሰ አድርገው ለማቅረብ የሚጥሩ በርካታ ደራስያን በመድረክ ብቅ ብለዋል፡፡ ከእነዚህ ደራስያንም ቢሆን ብዙ ነገሮችን መማር ስለሚቻል፤ ያልፃፋችሁ፤ ፃፉ፤ አንዱ ያጎደለውን፤ ሌሎቻችሁ ሙሉበት ከማለት ወደኋላ አልልም፡፡ የሚጻፉትን መጽሐፎች በበለጠ የተሟላ የሚያደርገው ግን፤ የሚያነቡና፤ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ወይም የተሰተካከለ መረጃ ያላቸው ሰዎች፤ ወይም የታሪክ ምሁራን ከጥናታቸው በመነሳት በመጽሐፎቹ ላይ ግምገማ አድርገው ሃሳብ ሲሰጡንና፤ እንደኔ ያሉ ተራ ዜጎች ደግም በሚሰጡት ትችት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ከዚህ እምነትም በመነሳት ነው ይህችን ትችት ጫር ያደረግኩት፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ "እኛና አብዮቱ" በሚል ርእስ መጽሐፍ ጽፈው በማሳተማቸው ያለኝን አድናቆት ልገልጽ እወዳለሁ፡፡ የጊዜያዊ አስተዳደር ደርግን በተመለከተ፤ እስከዛሬ ካነበብኳቸው በርካታ መጽሐፎች ያላገኘኋቸውን ትምህርቶች አግኝቸበታለሁ፡፡ በርካታ ጥያቄዎችንም ጭሮብኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን "የሰውን ልጅ ጊዜ ያስተምረዋል የሚለውን" ጽንሰ ሃሳብ እንድጠይቅ አድርጎኛል፤ ሁሉም የሰው ልጅ ከስራው፤ ከታሪኩና፤ ከሕዝብ ለመማር የማይችል መሆኑንም ይህ መጽሐፍ አረጋግጦልኛል፡፡ ከዚህ መጽሐፍ የተማርኩት አብይ ነገር፤ ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ከ17 ዓመታት የስልጣን ጊዜያቸው በኋላና፤ ከ20 ዓመታት በላይ ከታሰሩ በኋላ እንኳን፤ ከስራቸውና ከድርጊታቸው ምንም ያልተማሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ልክ እንደሳቸው፤ ምን ያህሉ የደርግ አባላት ከስራቸውና ከአሰቃቂ ታሪካቸው ትምህርት እንዳልወሰዱ ለማወቅ አዳጋች ነው፡፡ ራሱን የቻለ ጥናት ያስፈልገዋል፡፡ ኮሎኔል መንግሰቱ ኃይለማርያም "ትግላችን" በሚለው መጽሐፋቸው፤ ያስተማሩኝ ነገር፤ ዛሬም ከታሪክ ያልተማሩ የደናቁርት ሊቅ መሆናቸውን ነው፡፡ የመንግስቱ ኃይለማርያም ቀኝ እጅ የነበሩትና፤ ዛሬም ኮሎኔሉን "ታላቁና ብልሁ መሪያችን" ለማለት የሚዳዳቸው፤ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር፤ መጽሐፋቸው ያሳየኝ፤ ሻምበሉ ገና ከሶቭየት ሕብረት ትምህርታቸውን ጨርሰው የተመለሱ የመቶ አለቃ የአየር ኃይል መኮንን ከመሆን ለአንዲት ቀናት እንኳን ጊዜ ፎቀቅ እንዳላደረጋቸው ነው፡፡ ዛሬም በኢሕአፓ ላይ ቂም መቋጠራቸውን ነው መጽሐፋቸው የሚያሳያው፡፡ የመጽሐፉ ርዕስም በስህተት ይመስለኛል "እኛና አብዮቱ" የሚል ስያሜ የተሰጠው፡፡ እኛና ኢሕአፓ የሚል ርዕስ ቢሰጠው፤ የመጽሐፉን ይዘት ይበልጥ ይገልጠው ነበር፡፡

ሻምበሉ ከነመደምደምያው በ20 ምዕራፍ የከፈሉት ባለ-450 ገጾች መጽሐፍ፤ የደርግ ደመኛ ጠላት የነበረውን ኢሕአፓን በሕዝብ ለማስጠላት የተፃፈ ለመሆኑ ለማንም አንባቢ ፍንትው ያለ እውነታ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ፍቅረሥላሴ ዛሬም ጦርነታቸው ከኢሕአፓ ጋር ይመስላል፡፡ ዛሬም ቢችሉ ኢሕአፓ ብለው የሚጠረጥሩትን ሁሉ ከዛው ከአራት ኪሎ ቢሮዋቸው፤ መትረየስ ደግነው ቢረፈርፉት እርካታን እንደሚሰጣቸው አልጠራጠርም፡፡ ኢሕአፓ የሰራውም፤ ያልሰራውም በመጽሐፋቸው ላይ ተዘርዝርዋል፡፡ ሌላው ቢቀር ኢሕአፓ በጠራራ

ፀሐይ ገደላቸው የተባሉ ዜጎች ስም ዝርዝሮች በመጽሐፉ ተካተዋል። ምናልባትም ፍቅረሥላሴ፤ ከሶማልያው የውጭ ወራሪ ሃይል የበለጠ ኢሕአፓን በጠላትነት እንደፈረጁት፤ በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጠውታል።

ሻምበሉ፤ ደርግ ሥልጣን የያዘበትንና፤ ለ17 ዓመታት ረግጦ የገዛበትን ምክንያት፤ ፍትሃዊ እንደነበር ለማሳየት ሞክረዋል። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ውድቀት በኋላ ደርግ ስልጣን ለመያዝ ብቸኛ አማራጭ እንደነበር፤ ቢያስረዱንም፤ ለ17 ዓመታት ግን ለምን ብቸኛ አማራጭ ሆኖ እንደቀጠለ ያስጨበጡን ግንዛቤ፤ ዛሬ ኢሕአዴግ ከሚሰጠው ተልካሻ ሰበብ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ይላሉ እንዲህ ነው። የሁለቱም ምክንያት 'የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪውን ለመምረጥ ዝግጁ አይደለም' የሚል ነው። መጽሐፉ ብዙ ግድፈቶች አሉት፤ ብዙ ሸፍጥም ተላብሰዋል። በጣም የሚገርመው፤ ለደርግ፤ በተለየም አባቴ "የሞት መላእክ" ብሎ ለሰየማቸው ለኮሎኔል መንግስቱ፤ ግፍ የተመላበትና አሰቃቂ እርምጃ፤ ፍቅረሥላሴ ጥፋተኛ አድረገው የሚቆጥሩት የደርግ ሰለባ የሆኑትን ንጹሃን ዜጎች መሆኑ ነው። ይህ የታሪክ ሸፍጥ ራስን ከታሪክ ዳኝነት ለማዳን፤ በተጠቂዎቹ ላይ እንደገና የተሰነዘር ሕሊና ቢስ ጥቃት ነው። ለምሳሌ፤ ሻምበል ፍቅረሥላሴ፤ ጄኔራል አማን አንዶምን ለማዋረድና፤ በኤርትራ ባንዲራ ለመጠቅለል ያደረጉት ሙከራ እጅግ አሳፋሪ ነው። ጀግናውና ቆራጡ ጄኔራል አማን አንዶም፤ በደርግ ፋሽስታዊ ስርዓት በመጀመርያ ከተገደሉት 60 የሃገራችን ታላላቅ ሰዎች መሃል አንዱ ሆነው ሳለ፤ ፍቅረሥላሴ በድፍረትና በአሳፋሪ መልኩ፤ ለ60ዎቹ ኢትዮጵያውን መገደል ጥፋቱ የጄኔራል አማን አንዶም እንደነበር ነግረውናል።

በተጨማሪም፤ በለውጡ መጀመርያ አካባቢ፤ ኮሎኔል መንግስቱ በአብዛኛው የደርግ አባላት ድምጽ ከመሪነት ቦታቸው ሲወገዱና፤ ለጄኔራል ተፈሪ ባንቲ፤ የስም መሪነት ብቻ ሳይሆን፤ ትክክለኛና እውነተኛ የመሪነት ስልጣኑ እንዲሰጣቸው ሲወሰን፤ ፍቅረሥላሴ፤ ኢሕአፓ በአቋራጭ ስልጣን ያዘ በማለት፤ የደርግ አባላት በኮለኔሉ አምባገነንት በመበሳጨት የኮሎኔል መንግስቱን ስልጣን ለመገደብ የወሰዱትን እርምጃ ያጣጥሉታል። መንግስቱ፤ ከኮለኔል ዳንኤል አስፋው ጋር በመመሳጠር፤ ለፈፀሙት መፈንቅለ ስልጣንና፤ በእነ ጀነራል ተፈሪ ባንቲ ላይ ለወሰዱት አረመኔያዊ እርምጃ፤ ሻምበል ፍቅረሥላሴ ጥፋተኛ የሚያደርጉት እነ ጀነራል ተፈሪ ባንቲን ነው። ለሻምበሉ፤ ኮለኔል መንግስቱ አማራጭ ያልነበራቸው መሪ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ የሶማልያ ጦር አይሎበት ወደ ኋላ ያፈገፈገውን ምስኪን ወታደር፤ በኮሎኔል መንግስቱ መሪነትና ትእዛዝ ከጀርባው በጥይት እንዲቆላ መደረጉን፤ በመጽሐፋቸው ሲነግሩን የመንግስቱ ኃይለማርምን ቆራጥና ብልህ መሪነት ተምሳሌት እንደሆነ አድርገው ነው። ይህ ለእኔ የጠቆመኝ ነገር፤ ሻምበሉ ያሰከራቸው የንጹህ ዜጎች ደም ገና ያልበረደላቸው መሆኑን ነው። ጸሃፊው የደርግን ነፍሰ ገዳይነት፤ እንደ ታላቅ አኩሪ ገድል፤ ሲተርኩ የሚሰማቸው ኩራት በመጽሐፉ ውስጥ እንደ ጠዋት ብርሃን ቁልጭ ብልዋል።

መጽሐፉ በደርግ የ17 መሪር የአገዛዝ ዘመን፤ በአገዛዙ የተፈፀሙ አንኳር ወንጀሎችን ሳይጠቅስ ያለፈበት ምክንያት ምን እንደሆነ ፀሃፊው ቢያንሰ ማብራረት ነበረባቸው። ይህ ግን አልተደረገም። ከሁሉም የሚገርመውና የሚያሳዝነው፤ ፍቅረሥላሴ፤ በቀይሽብር፤ በነፃ እርምጃ፤ እንዲሁም በተለያየ ሰበብ በእሳቸውና በጓዶቻቸው መሪነት ስለተጨፈጨፈው የሃገሪቱ ብርቅዬ ዜጋ ምንም አለማለታቸው ነው፤ ምንም እንኳን እነ ጄነራል ተፈሪ ባንቲ፤ ያለምንም ፍርድ፤ በመንግሰቱ በችኛ ትእዛዝ፤ እዛው ቤተመንግሰት ምድር ቤት ውስጥ እንደተረሸኑ ቢነግሩንምና ግድያው ተገቢ እንደሆነ ቢያወድሱም፤ ኮሎኔል አጥናፉ ለምንና በምን ሁኔታ እንደተገደሉ፤ ፍቅረሥላሴ አልነገሩንም። በአፄ ኃይለሥላሴ የእርጅና ዘመን በወሎ ሕዝብ ላይ በደረሰው አሰቃቂ ጠኔ፤ በንጉሡና በአስተዳደራቸው ላይ እርግማን ያኾጎደጎዱት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒሰትር፤ በእሳቸውና በጓደኞቻቸው የግዛት ዘመን እአአ በ1984 በሃገራችን፤ ምናልባትም በዓለም ታይቶ የማይታወቅ ጠኔ ሕዝቡን ሲፈጀው፤ እሳቸውና ጓደኞቻቸው

የ10ኛውን ዓመት የግዛት በዓላቸውን ለማክበር ውስኪ ሲራጨበት የነበረውን አሳዛኝና አሳፋሪ የታሪክ ምዕራፍ፣ በ450 ገፆች ውስጥ የአንድ መስመር እንኳን ቦታ አልሰጡትም። ይህን ብቻ አይደለም፣ ሻምበሉ፣ እነሱና አብዮታቸው ከሰሩት ወንጀል ውስጥ መጽሐፋቸው የገደፈው። ፍቅረሥላሴ የ1981 ዓም. መፈንቅለ መንግሰት ሙከራን አስመልክቶ የተናገሩት ምንም ነገር የለም። ሻዕብያ፣ "ደርግ፣ ቀኝ እጁን ቆረጠ" ብሎ የተሳለቀበትን የጀግናውን የጄኔራል ታሪኩ ላይኔን ግድያ፣ ፍቅረሥላሴ ለምን ሳይጠቅሱ እንዳለፉ ሌላው እንቆቅልሽ ነው።